# ይድረስ ለወያኔ የፓለቲካ ወያላዎች ሁሉ

ከኃይለ ልዑል ግርማ
ዋሽንግተን ዲሲ

ማንነታቸውን የደበቁ መስሏቸው "የማያድግ ልጅ አይርገምህ የማይሞት ሽማግሌ አይጥላህ" በሚል ርዕስ ከወያኔ የፖለቲካ ወያላዎች የተጻፈውን ከንቱ ጽሑፍ ተመለከቼ፤ አንዲት ከመቶ እንኳን እውነትነት የሌለውን አሉባልታ፣ ብልግናና ሀሰት የተሞላበትን ልፈፋቸውን አንብቦ መልስ መስጠት ቀርቶ መረዳት እንኳን የሚያዳግት ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: ከላይ የተጻፈው ዝቅ ብሎ ከተጻፈው ጋር የሚቃረን የጻፉትን እንኳን መልሰው ያላነበቡት ያው የምናወቃቸው የወያኔ የፖለቲካ ወያላዎች ናቸው:: እነ ዳዊት ከበደና ጋደኞቹ::

አዬ ኪሳራ እንዲህ ዓይነት ተራ አባባል ውስጥ ያስገባቸው በተለጣፊ ፉርጎ ላይ ያሉት አባሎቻቸው ወራጅ አለ በሚሉበት ወቅት ሌላ ተሳፋሪ ለማስገባት ያደረጉት ቢሆንም የከዚህ ቀደሙ ሴራቸውና ሙከራቸው ሁሉ አንድ በአንድ እየተጋለጠ ስለከሸፈባቸው ዛሬም እንደለመዱት ግራ የሚጋባና የሚከተላቸው ያለ መስሏቸው ነው:: አይሰራም:: "የፋራ ፖለቲከኛ" ሁሉ ዛሬ ነቃ !

በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት አመራር ላይ የተጀመረው የአፍራሽ ቅስቀሳ በመቀጠል ዛሬ ያልለከፈው ሰውና ክፍል የት ይገኛል? እውነት ተደብቃ አልቀረችምና ብቅ ስትል ያ ሁሉ የሀሰት ፕሮፓጋናዳ አፈር ከድሜ ሲገባላቸው በወጥመድ እንደተያዘች አውሬ አይናቸው ቁልጭ ቁልጭ በማለት ያደፍጣሉ:: በስም ማጥፋት የተለከፉት ካድሬዎቻቸው ደግሞ ሲሰለጥኑም በስድብና በብልግና ነውና የተለመደ ጸያፍ ስድባቸውንና መረን የለቀቀ አባባላቸውን ቀጥለውበታል::

ዛሬ ግን ዝም ብሎ የሚታዩበት ጊዜ አክትሟል:: በአጭሩ በግልጽ መቀመጥ ያለበትና በግልጽ መነገር ያለበት እውነታን ለሕዝብ ማሳወቅ ደግሞ የአንድነት ኃይሉ ክፍል ኃላፊነት ነው:: አሁን ጎራው ለይቷል:: የአንድነት ኃይልና የጸረ አንድነት ኃይል:: የጸረ አንድነት ኃይል ክፍል ውስጥ የወያኔ እድሜ በማንኛውም ዓይነት ሁኔታ እንዲቀጥል የሚፈልጉ ክፍሎች "ከወያኔ ጋር በአብሮ መስራት ይቻላል"፣ "መስመራችን ትክክል አልነበረም" በሚል፣ "መቻቻል" በሚሉት የእጅ መስጠት ስም፣ "ብሔራዊ እርቅ" ወዘተ.... እያሉ የሕዝብን ትግል ለወያኔ ለመስጠትና ታማኝ ተቃዋሚ ሆኖ የወያኔን እድሜ ለማራዘም የሚደረግ ዘመቻ ነው:: የአንድነት ኃይሉ ደግሞ ሀሰቱን በማጋለጥ፣ ሐቀኛ ኢትዮጵያውያንን ስም በማስጠበቅ፣ የሕዝብን ትግል አናስነጥቅም በማለት፣ ለሀገሩና ለሕዝቡ ተሚጋችና ተከራካሪ ሆኖ እየታገለ ይገኛል::

ሐቅን እያወቁ በየቀኑና በየሳምንቱ የወያኔ ፖለቲካ ወያላዎች አፍራሽ ቅስቀሳ በካሄዱ ቁጥር ግራ የሚጋባ፣ ሻዕቢያው ኤልያስ ክፍሌ አንድ የሀሰት ጽሑፍ በለጠፈ ቁጥር "አልሰማህም እንዴ እንዲህ እኮ ተባለ" እያሉ የሚያደነቁሩንን ተላላኪዎች ማሳፈር ካልቻልን፣ ትግሉን የከዱ የተለጣፊ ቡድን ሰዎች ፓልቶክ ክፍል ወይም በሬዲዮ ብቅ ብለው በለፈለፉ ቁጥር የምንዋዥቅ ካለን ያለምንም ጥርጥር የወያኔ የፕሮፓጋንዳ ሰለባ ሆነናልና ሌላውን ሳይሆን እራሳችንን መጠየቅ አለብን:: አንዴ መታለል ይቻላል ሁለቴም ካለማስተዋል ሊደገም ይቻላል ከዚያ በላይ ግን እጅግ ተላላነት፣ አለማስተዋልና ወዶ ገባ ሊያደርገን ይችላልና ሕሊናችንን እንጠቀምበት::

ወደ ዋናው ጉዳይ ልግባ:: ቅንጅት እንዲዳከም፣ ቅንጅት እንዲከፋፈል የሚፈልግ ማነው? ብለን እንጠይቅ እስቲ:: መልሱ ግልጽ ነው:: ወያኔ ብቻ ነው:: ታዲያ ለቅንጅት መከፋፈል ዋና ተዋናይ የነበሩት አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ብርሃነ መዋ፣ ዶክተር ሞገስ ገብረማርያምና ሌሎቹም መቼ ነው ቅንጅት እንዳይከፈል ጥረት ያደረጉት፣ የተጨነቁት፣ ያሰቡት? አንድም ቦታ የለም:: አንድ በሉ:: ከዚህ በፊትም ብዙ ጊዜ ይህ ምሳሌ ተጠቅሷል::

ልጁ የኔ ነው ብላ ያልወለደችውን የሌላ ሴት እናት ፍላጎትን ነው በግልጽ ያንጸባረቁት። ሴትዮዋ ያልወለደችው ልጅ የእርሷ እንዲሆን በመፈለግ እንዲሰጣት ካልሆነም በሰይፍ ተቆርጦ ግማሽ አካሉን ለመውሰድ እሺ አለች። በዚያው ዓይነት ቅንጅት በተፈለገው የወያኔ መልዕክተኞች እጅ ከገባ፣ ሰላም ወረደ ተብሎ ሁኔታዎችን አመቻችተው በ2010 ምርጫ ላይ የታማኝነታቸውን ሚና ተጫውተው ትንሽ የሥልጣን ፍርፋሪና ጥቅም አግኝተው የወያኔን እድሜ ማራዘም ነው።

የእነርሱ የበላይ የሆነውና የሴራው መሪ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ፣ ተከታዮቹ እነ ብርቱካን፣ አቶ ብሩክ፣ አቶ ግዛቸውና ዶክተር ኃይሉ አርዓያ ከሁለት ዓመት በፊት እነአንዳርጋቸው የጀመሩትን የመከፋፈል ስራ በማጠናከር በየትም ቦታ ችግሩን ለመፍታት ውይይት ሳያደርጉ የራሳቸውን ቡድን አጠናክረው፣ ሕዝቡን ግራ አጋብተውና ገንዘቡን ሰብስበው የግል ዓላማቸውን ለማራመድ ሞከሩ እንጂ ስለ ቅንጅት አለመከፈልና መጠናከር ጉዳያችን ነው አላሉም። ምክንያቱም ዓላማቸው ቅንጅትን ተቆጣጥረው ለወያኔ ታማኝ ቅንጅት ለማስረከብ ስለሆነ ነው። ዶክተር ብርሃኑ ነጋ በዲሴምበር 3 ቃለመጠይቁ ላይ ይህንን ግልጽ አድርጎ ቅንጅት ለሁለት እንዲከፈል ተናግሮት ጨርሶታል። ዶክተር ብርሃኑ ነጋ በውጭ የጠላት መንግሥት አማካኝነት የተተከለ የወያኔ እድሜ ቀጥል መሳሪያ ነው። የሚያሳዝነው የወያኔ ቫይረስ በደሙ ውስጥ ተገኝቶ እንደወያኔ እርሱም መሰሎቹ ላይ ማተኮሩና አንዳንዶቹን ማሳሳቱ ነው። አሳፋሪ ተግባር። ጠባብነት ወይም ዘረኝነት በራስ ላይ የተጠመደ ፈንጂ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ እሺ አይላቸውም።

ለማስታወስ ያህል ከምርጫው በኋላ በመስከረም ወር 2005 ላይ አባይ ፀሐዬ ዋሽንግተን መጥቶ ለወያኔ ደጋፊ አባሎቹ በምስጢር ቅንጅትን ደምስሰን ታማኝ ቅንጅት እንፈጥራለን ብሎ ተናግሮ ነበር። ወያኔ በታማመነበት ተማምኖ ነው እንዲያ ያለው።

የወያኔን ባህርይና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የማጥፋት ሴራና ተንኮል የሚዘነጋ ካለ ትግሉ መድረክ ላይ መውጣት የለበትም። የሚጠቅመው እነርሱኑ ነውና። ወያኔ በመጀመሪያ የፈለገው ከተቃዋሚ መሪዎች መካከል ሰዎችን በመምረጥ ተቃዋሚውን ክፍል በቀላሉ መቆጣጠር ነው። በዚህም መሰረት ነው ለዶክተር ብርሃኑ ነጋ የበረከት ስምዖን ጋደኛ ኃላፊነቱን የሰጡትና ቅንጅትን ለዚህ አደጋ ያበቃው። ዶክተር ብርሃኑ ሌሎች የቅንጅት መሪዎች ወያኔን ለመጣል ደፋ ቀና ሲሉና ከሕዝቡ ጋር ሲወጡ ሲወርዱ አጅሬ በቀላሉ ቅንጅትን የሚቆጣጠርበት መንገድ ለካስ አዘጋጅቶ ኖሯል። የቀስተደመና አዲስ አባል የሶስት ሳምንት የአባልነት እድሜ ያላትን የቅንጅት መሪ እንድትሆን አበቃት። ወይዘሮ ብርቱካን ከዚያ በፊት ያ ሕዝብ ሲሰቃይ መከራውን ሲያይ እርሷ በወያኔ ፍርድ ቤት የዳኝነት ወንበር ያገኘች ሰው መሆኗን መዘንጋት የለብንም። የፍትሕ ሥርዓቱ ለወያኔ ታማኝ በሆኑና ብቃት በሌላቸው ሰዎች ለመተካት የተደረገውን ደባና የተንኮል ሥራ ማስታወስ ይገባናል። ብርቱካን ታዲያ የት ነበረች ምን ስትሰራ ከረመች? እስከ መስከረም 1998 ድረስ ? አቶ ሰዬ አብርሃን በዋስ ለቀቀች ስለተባለ የትግል መለኪያ ሆኖ ነው የቅንጅት መሪ ለመሆን የበቃችው? ብርቱካን ሜዲቅሳ እነ ብዙ ወንድማገኝና ሌሎች ካድሬዎች እንደሚሏት የፓርላማ ተመራጭ አይደለችም። የሕዝብ ድምጽ የላትም። የሰፈርዋ ሰዎች ቅንጅትን ሲመርጡ እርሷ ቅንጅትን መምረጧ አይታወቅም። እንዲያውም በምርጫው ወቅት ከከፍተኛ የወያኔ ባለሥልጣን ጋር በፈጠረችው የወዳጅነት ግንኙነት ነፍሰ ጡር ነበረች ወዲያው የሴት ልጅ እናት ሆነች። ከቤተሰቦቿና ጎረቤቶቿ በቀር ማን እንደሆነች የሚያውቃት አልነበረም። እድሜ ለብርሃኑ ነጋ መስከረም አምስት የቀስተደመና አባል አደረጋት መስከረም 24 የቅንጅት ምክትል ፕሬዚዳንት እንድትሆን አበቃት። ስንቴ ነው የምንታለለው? የብርቱካን ወደ ቅንጅት አመጣጥ ታሪኩ ባጭሩ ይሄ ሲሆን ዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንድትመራ ሰዎች ይነግሩናል። በህግ አምላክ እንበላቸው።

የብርቱካንን ባዶ ዝና የፈጠሩላት እነ አንዳርጋቸው ጽጌ አቀነባብረው ከቃሊቲ እስር ቤት ለአሜሪካ አምባሰደር ጻፈችው በተባለው የሀሰት ደብዳቤ አማካኝነት ነው። እስር ቤት እያለች ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሆን ስለጸጉሩዋ ውበት የበለጠ ትጨነቅ እንደነበር ይታወቃል። እንዲህም አድርጎ መሪ የለም። እድሜ ለብርሃኑ ነጋ።

በኢትዮጵያ ሪቪውና በኢትዮፎረም ዳዊት ከበደ ድጎረ ገጽ ላይ የወጣው ጽሑፍ ለፕሮፌሰር አሥራት መታሰርና መሞት፣ ለዶክተር ታዬ መታሰር፣ በምርጫው ሳቢያ ለተገደሉት ወጣቶች ሁሉ ተጠያቂ ያደረገው የተከበሩ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የቅንጅት ፕሬዚዳንትን ነው። ያስቃል። የጹሁፉ ባለቤት ወይም ባለቤቶች የወያኔ ቅጥረኞች ወይም የፖለቲካ ወያላዎች ለመሆናቸው ሌላ ምንም ማስረጃ አያስፈልግም። ያንን ሁሉ ወንጀል የፈጸመውን ወያኔን ላለመንካት ወንጀሉን ሁሉ ለመደበቅ ሲሉ በቅንጅት ፕሬዚዳንት ላይ ደፈደፉት። ሞታቸውን ተመኙላቸው። ዛሬም እናስታውስ የሃምሳ ሁለቱ ገጽ የወያኔን የውጭውን ትግል ለማፈንና ለማዳፈን ያዘጋጀውን ማንዋል እና 40 ና 50 ሚሊዮን ዶላር ሥራውን እየሰራ ነው። ለአጋዚ ጦር ትእዛዝ ሰጥተው ከሁለት መቶ በላይ ሰው ያስገደሉት የቅንጅት ፕሬዚዳንት ናቸው ይሉናል ነገ። ምክንያቱም አለቃቸውን መለስ ዜናዊን ከሃላፊነትና ተጠያቂነት ለማዳን ሲሉ ቆራጥና ጀግናው ኢትዮጵያዊውን ኃይሉ ሻውልን በገመዱ ማስገባት አለባቸው። ከዚህ በላይ ወያኔነት ምን አለ?

በአምስቱ የቅንጅት አመራር ላይ ባደረጉት የመከፋፈልና የጥፋት ሴራ፤ የቅንጅትን ፓርቲ ለአደጋ በማጋለጣቸው ጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ እስኪሰጥ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ በቅንጅት ስም እንዳያደርጉ መታገዳቸው ትክክለኛና አግባብ ሲሆን፤ አለበለዚያማ ስንት ህይወት የጠፋበትን፣ ስንቱ የታሰረበትንና የተሰደደበትን ፓርቲ ሲጠፋ ማየት ፕሬዚዳንቱንም እኮ ተጠያቂ ያደርጋቸዋል። ቆራጥ መሪ ማለት አስቸጋሪ ሁኔታ ሲመጣ ውሳኔና አመራር መስጠት የሚችል ማለት ነው። ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ያደረጉት ያንን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ደስ ብሎት ተቀብሎታል። ደጋፊው ሁሉ ትክክል ነው እሰይ እልል ብሏል።

የነዳዊት ከበደ መቀባጠር ያልተጠበቀ ጉድ አወጣ። የቅንጅት አመራር ፓርላማ እንዳይገባ ያደረጉት ፕሬዚዳንቱ ናቸው ማለታቸው ስንት ልደቱ አያሌዎች ቃሊቲ አላግባብ መክረማቸው አንገብግቧቸው ኖራል። ታዲያ ማንን እጅ እግራቸውን ያዘው? ፓርላማው እኮ አጠገባቸው ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፓርላማ እንዳይገቡ የነገራቸውና ያስጠነቀቃቸውን ዘንግተውታል። አሳፋሪዎች። ቆራጡና ጀግናው ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ግን የሕዝብን ፍላጎትና ቃል መጠበቅ እንጂ ሌላ ወለም ዘለም የሚል ዓላማ የሌላቸው አኩሪ መሪ ናቸው። አሁን ግልጽ የሆነው ቃሊቲ ለ20 ወራቶች የታሰሩት በእርሳቸው ጥፋት ነው ለማለት ከሆነ፤ መለስ ዜናዊ አይጨቅንም የሃያ ወራቶች የፓርላማ ደሞዛችሁን አስከፍሎ ሊያስገባችሁ ይችላልና ቀጥሉበት።

ከአሁን ወዲያ ይህን በዚህ የስም ማጥፋት ዘመቻ ላይ የተሰማራችሁ የወያኔ የፖለቲካ ወያላዎች ሁሉ ልትጠነቀቁና ልታስቡበት የሚገባ አንድ ነገር አለ። ሥራችሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ እየተከታተለ ነው። አንቅሮ የሚተፋችሁና ቁጣውን የሚገልጽበት ቀን እየተፋጠነ ነው። የሕዝብ ቁጣና ኃይል ደግሞ ዘንግታችሁት ከሆነ ሚያዝያ ሰላሳ ቀን 1997 ዓ.ም ግልብጥ ብሎ የወጣው የሕዝብ ማዕበልን ልታስታውሱ ይገባል። ያ ሕዝብ ደግሞ መሪዬ ብሎ የሚያምነውና የተቀበለው ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን ነው። አይደለም ብርሃኑ ነጋን አይደለም ብርቱካን ሚዴቅሳን። እነርሱንማ ሕዝብ ተፍቷቸዋል። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሕዝብ የጸረ ወያኔ ትግሉን አቅጣጫ እንዲቀይርና ተከፋፍሎ ቅንጅትን ለማጥፋት መሳሪያ በመሆናቸው ከወያኔ ጎራ መድቧቸው ቀን እየጠበቀላቸው ነው። ተከታዮቻቸውም እንደዚያው። የወያኔ የፖለቲካ ወያላዎች መሪዎች እንደ አዲስ አበባ ታክሲዎች የሞላ የሞላ እያሉ በተለጣፊው ፉርጎ ላይ ሆዳሙን፣ አድር ባዩን፣ ፈሪውን፣ ባንዳውን ለመጫን የሚያደርጉት ሙከራ ከሽፏል። መሪያቸው የተለጣፊውን ፉርጎዎቹን "ወደፊት የሚገፋበትን ስሌት ለማሰብ" አሜሪካ መቆየቱም እራሱን የቻለ ጉድ አለበት። ሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ።